CURRENT AFFAIRS HOME

# ከሁለት መቶ ሰባ ሺ በላይ ተፈናቃዩች በደሴ ከተማ በችግር ላይ ይገኛሉ

By wazemaradio

SEP 17, 2021



ዋዜማ ራዲዮ- በሰሜን ወሎ የሕወሓት አማፅያን የከፈቱትን ማጥቃት ተከትሎ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው ወደ በደሴ ከተማና ጊዜያዊ መጠለያዎች ሸሽተው የሚገኙ ነዋሪዎች ሁለት መቶ ሰባ ሺ ሶስት መቶ ያህል መድረሳቸውን የደሴ ከተማ ምክትል ከንቲባ አበበ ገብረመስቀል ለዋዜማ ተናግረዋል፡፡

በ12 የመንግስት ትምህርት ቤቶች ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሀያ ዘጠኝ ሰዎች እንዳሉ የተናገሩት አቶ አበበ የተቀሩት በዘመድ ቤት እንዲሁም ቤት ተከራተው እየኖሩ ነው ብለዋል ፡፡

ለተረጂዎች በፈቃደኝነት ድጋፍ እያሰባሰቡ ያሉ ግለሰቦችና የመብት ተሟጋቾች “ መንግስት ለተረጂዎች ድጋፍ እያቀረበ አይደለም” ፣ “ ተፈናቃዮች ተረስተዋል” ሲሉ የመረረ ቅሬታቸውን ለዋዜማ ሪፖርተር ተናግረዋል፡፡ አሁን በደሴ ከደረሰው ረሀብ በተጨማሪ የትራኮማ በሽታ ወረርሽኝ መከሰቱንም የከተማዋ በጎ ፈቃደኞች ያስረዳሉ፡፡ የተረጂዎች ቁጥርም ከአራት መቶ ሺህ በላይ መሆኑን ተሟጋቾቹ ይናገራሉ፡፡

ተፈናቅለው ደሴ ከተማ የተጠለሉት ዜጎች ለከፋ የምግብ ዕጥረት መጋለጣቸውን ያልሸሸጉት የከተማው ምክትል ከንቲባ አቶ አበበ ገብረመስቀል ለችግሩ ተጠያቂ መሆን ያለበት ነዋሪዎቹን ከቀዬቻው ያፈናቀለው ሕወሓት ነው ባይ ናቸው፡፡

መንግስትና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች እስካሁን ለ178 ሺ ተፈናቃዮች ዕርዳታ አድርሰዋል፡፡ የአለም የምግብ ፕሮግራምም አስቸኳይ ዕርዳታ ዕደላ በመጀመሩ በርከት ያሉ ተፈናቃዮች ድጋፍ እንደሚያገኙ አቶ አበበ ያስረዳሉ፡፡

መንግስት ዕርዳታ በማቅረብ በኩል የመሪነቱን ድርሻ ይዞ እየሰራ ነው የሚሉት ምክትል ከንቲባው ከተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ህብረተሰቡ እያደረገ ያለው ድጋፍ ለተጎጂዎች መድረስ ጀምሯል ብለዋል፡፡

ከተረጂዎች ቁጥር አንፃር እርዳታው በቂ አለመሆኑንና ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልግም አቶ አበበ አሳስበዋል፡፡

## CATEGORIES


About Wazema

Art and Culture

Benegerachin Lay-Discussion

Book Review

Current Affairs

Fake News alert

Home

Letter From Addis

News

PODCASTS

Talking points

Uncategorized

Video

Wazema Dossier

Wazema Forum


## WAZEMA MEDIA


Wazema Media is legally registered organization founded in 2014 by Ethiopian exiled journalists, currently based in Addis Ababa, Ethiopia.

